# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – hello@ethiogodslove.org አዘጋጅ፡- መላኩ ማሞ ትዕዛዙ

**ጥቅምት** 1996 Oct. 2003 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" (ኢሳ 54÷13)

**www.EthioGodslove.org**

# ይቻላል

"ቢቻለኝ ወንጌላዊ እሆናለሁ"
"ቢቻለኝ ነግጄ እከብራለሁ"
"ቢቻለኝ ከድኅነት እወጣለሁ"
"ቢቻለኝ መልካም ምኞቴን እፈጽማለሁ"
"ቢቻል ከሐገሬ ረሐብን አስወግዳለሁ"
"ቢቻለኝ ተምሬ ራሴንና ሐገሬን እጠቅማለሁ፡ ወዘተ"

**"ኢየሱስም፡- … ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው።" (የማርቆስ ወንጌል 9÷23)**

በርክሌይ በሚገኘው የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ÷ በሒሳብ ለመመረቅ እማር ነበር። አንድ ቀን እንደ ልማዴ ሰዓት አሳልፌ ክፍል ስገባ÷ ጥቁር ሰሌዳው በሒሳብ መልመጃ ሞልቶ ቆየኝ። እኔም የቤት ሥራ ሳይሆኑ አይቀሩም ያልኳቸውን ሁለት ጥያቄዎች በቶሎ ደብተሬ ላይ ቀዳኋቸው። ያንኑ ዕለት ቤቴ ገብቼ ለመሥራት ስሞክር÷ በሕይወቴ ዘመን ካየኋቸው ሒሳቦች ሁሉ ይበልጥ ከባድ ሆነው አገኘኋቸው።ሁለቱንም ጥያቄዎች ለመፍታት በየዕለቱ ባለመሰልቸት ሙከራ አደረግሁ። ቀናት አልፈው ቀናት ሲተኩ ምንም መልስ አላገኘሁም። ዳሩ ግን ተስፋ ባለመቁረጥ ለመፍታት ጨከንሁ።

ከብዙ ቀኖች ጥረትና ድካም በኋላ ተሳካልኝ። ሁለቱንም ጥያቄዎች ፈታኋቸው። በነጋታውም ወረቀቴን ወደ ትምሕርት ቤት ወሰድሁት። ክፍል ውስጥ ስገባም ፕሮፌሰራችን በወቅቱ ሥራ ይበዛበት ስለ ነበረ÷"ጠረጴዛው ላይ አርገው"አለኝ። እኔም በጠረጴዛው ላይ የወረቀት ክምር ስለ ነበረ÷ ወረቀቴ እንዳይጠፋ እየሰጋሁ ከዳር አስቀምጬው ወጣሁ።

ከስድስት ሳምንት በኋላ ዕሑድ ጧት÷በሬ በኃይል ሲንኳኳ ባንኜ ተነሣሁ። በመደናበር በሩን ከፈት ሳደርግ ቆሞ ያገኘሁት ፕሮፌሰሬ መሆኑ ደግሞ የባሰውን አስደነገጠኝ። ደግሞም አለወትሮው ርጋታ አልነበረውም። "ጆርጅ! ጆርጅ!" "ፈታኸው እኮ" "ሒሳቡን እኮ ፈታኸው" እያለ ይጮኽ ነበረ።

እኔም ሒሳቡን መፍታቴን አውቅ ስለ ነበር÷አዎን፤ ምን ነው? መፈታት አልነበረበትም እንዴ? ብዬ በመገረም ጠየቅሁት። ከዚያም ፕሮፌሰሩ ሲመልስልኝ፡- "በሰሌዳው ላይ የነበሩት ሁለቱ ጥያቄዎች እኮ የቤት ሥራ አልነበሩም" አለኝ። ማብራራቱንም ቀጠለና "ሁለቱ ጥያቄዎች እስከ ዛሬ ድረስ የሒሳብ ልቃውንት መፍታት የተሳናቸው የታወቁት ጥያቄዎች ናቸው።እነዚህን መፍታትህ ተዓምር ነው÷ጉድ ነው፤በማለት መደነቁን ቀጠለ።

አስተውሉ ! እነዚህ ጥያቄዎች ሊቃውንት ሊፈቷቸው የተሳናቸው፡ የታወቁት ጥያቄዎች መሆናቸውን አውቄ በነበር÷ ሙከራ እንኳ ማድረጌን እንጃ። አይቻሉም፡ የሚል ዕውቀት ስላልነበረኝ ተግቼ ሞከርሁ። በመጨረሻም አይቻሉም የተባሉትን ጠያቄዎች ለመፍታት ቻልሁ።
/ጆርጅ ቢ. ዳንትዚግ/ (ጆርጅ ዳንትዚግ በእስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ÷ የኮምፒውተር ሳይንስና ኦፐሬሽንስ ሪሰርች÷ፕሮፌሰር ናቸው)

የሰው ልጅ ቀንደኛ ጠላቱ ÷ ያሰበውን መልካም ነገር ለማድረግ ኣለመቻሉን አምኖ መቀበሉ ነው።ከሁሉ የሚከፋው ደግሞ ተስፋ በመቁረጥ ዳግመኛ አለመሞከር ነው። የሚከተለው ተስፋ ያለመቁረጥ ምሳሌ ነው።

## ለሚያምን ሁሉ ይቻላል
(ማርቆስ 9÷23)

## የአንዲት ነርስ ምስክርነት

ነርስ መሆን በጣም እመኝ ነበር። የታመሙትን ሰዎች ረድቶ ሲፈወሱ ማየቱ እጅግ ይማርከኝ ስለ ነበረ ነው።ሆኖም ብዙ ማጥናት ስለማልወድና የትምሕርት ውጤቴም ጥሩ ስላልነበረ ምን እንደማደርግ ግራ ይገባኝ ነበረ። በአሥራ ዘጠኝ ዓመቴ÷ በነርስነት ትምሕርት የመጀመሪያውን ዓመት ወደቅሁ። በሚቀጥለውም ዓመት ደግሜ ወደቅሁ።

በነበርሁበት የነርስ ትምሕርት ቤት አንዲት የማልረሳት አስተማሪ ነበረች። በትምሕርቷ ጥሩ ውጤት ለማያሳዩት ተማሪዎች ብዙም ትዕግስት አልነበራትም። ስለዚህ እኔም በፊቷ ሞገስ አልነበረኝም። አንድ ቀን "ነርስ ለመሆን የሚያስፈልገውን ነገር ስለ ሌለሽ ብታቋርጪ ይሻልሻል" ብላ ፊት ለፊት የነገረችኝ አይረሳኝም።

ተስፋ የማስቆረጥ ቃሎቿ አእምሮዬ ውስጥ እየደወሉ ብዙ ጊዜ ያስፈራሩኝ ነበረ። ዳግመኛ ሞክሬ በወደቅሁ ጊዜ÷ እውነትም ነርስ መሆን አልችልም ብዬ ወደ ማመን ደረስሁ።በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የውርደት ስሜት ስላደረብኝ÷ ማንም ወደማያውቀኝ ወደ ሌላ ከተማ ተዘዋወርሁ። እዚያም በፀጥታ በመቆየት ራሴን አረጋጋሁ። ራሴንም የምችልበት ሥራ ማግኘት ስለ ነበረብኝና÷የሕክምናን ሥራ ስለምወድድ፡ በሕክምና መዝገብ ያዥነት በአንድ ሆስፒታል ተቀጠርሁ። ሥራውም ተስማማኝ። ሆኖም ነርስነትን ከሐሳቤ ማስወገድ አልቻልሁም።ከነርስነት በስተቀር ያረግሁትን ባደርግ እንደማልረካ ግልጽ እየሆነልኝ መጣ። ታዲያ ምን ያደርጋል÷ ከብርቱ ፍላጎቴ ጐን ተመጣጣኝ የሆነ የመውደቅ ፍርሐትም ነበረብኝ። አይቻልም ይቻላል÷አይቻልም÷ይቻላል፡- የሚሉት ሐሳቦች በአእምሮዬ ውስጥ ባለማቋረጥ ይፈራረቁ ነበረ።

ለአምስት ዓመታት በየዓመቱ ወደ ትምሕርት ለመመለስ ዕቅድ አድርጌአለሁ። በሞከርሁ ቁጥር አይቻልም÷አሁንም አወድቃለሁ የሚለው ፍራቻ ያሰናክለኝ ነበር። ምዝገባ በሚጀመርበት ጊዜ፡ ምክንያት ፈልጌ አስተላልፈው ነበረሁ። ከሥራዬ ጋር አይመቸኝም፤ በመሥሪያ ቤቴ እፈለግ እሆናለሁ ወዘተ እያልሁ ምክንያት አደርግ ነበርሁ።

ፍላጐቴ ሳይሟላ ዓመታት አለፉ። በመጨረሻም በራሴ በኩል ምንም ችሎታ እንደሌለኝ ስለ ተረዳሁ ÷ የእግዚአብሔርን ርዳታ ለመጀመሪያ ጊዜ መጠየቅ ጀመርሁ። ዓላማዬን ለመፈጸም የሚያስፈልገኝን ኃይል እንዲሰጠኝ መፀለይና መጽሐፍ ቅዱስንም ማንበብ አዘወተርሁ።

ከዚያም አንድ ሰው አእምሮን በቀና ሐሳብ የሚሞሉ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የተጻፉ መጻሕፍትን ዝርዝር ነገረኝ። እነርሱንም ገዝቼ በማንበብ፡ ቀስ በቀስ፡ በቀና አስተሳሰብና በተስፋ እየተሞላሁ መጣሁ። ዕምነቴ በኃይል አደገ። ተስፋና መተማመን ሕይወቴን እየሞላው ሄደ።በእግዚአብሔር ርዳታ የማይቻል ነገር እንደ ሌለ እያደር ዕምነቴ እየጠነከረ ሄደ።

በ1978 ዓም÷የነርስነት ትምሕርት ምዝገባ ሲጀመር በዕምነትና በተስፋ ተሞልቼ የኮሌጁን በር ከፍቼ ገባሁ። ፍርሐት ፍርሐት ብሎኛል? በእርግጥ ብሎኛል። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነውና አልፈዋለሁ የሚል መጽናናት ነበረኝ። ከሁለት ዓመት በኋላ ከመቶ ተማሪዎች፡ መሐከል፡ከአምስቱ የማዕረግ ተማሪዎች አንዷ ሆኜ ጨረስሁ÷እግዚአብሔር ይመስገን። ከዚያም ባለማቋረጥ ትምሕርቴን ተከታትዬ በመጨረስ÷እስከ አሁን ድረስ በነርስነት፡ አገለግላለሁ። ደስታዬም የተሟላ ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገን።

(ይህች እህት አሁንም በነርስነት ሙያ ተሰማርታ በመሥራት ላይ ትገኛለች።)

## "የየሱስ ሥዕል"



አንድ ወንድም በቤቱ አረፍ ባለበት ወቅት መጽሔት ያነብብ ነበር። ነገር ግን ትንሽዋ ልጁ እንዲያጫውታት ፈልጋ ትነዘንዘው ነበር።እርሱም ንባቡን በጸጥታ ለመቀጠል ልጅቷን ሥራ ለማስያዝ ብልሐት አሰበ። ከዚያም አንድ የዓለም ካርታ ያለበትን ገጽ ከመጽሔቱ አግኝቶ ገነጠለና÷ በብዙ ቦታ ቆራረጠው። ከዚያም ልጅቱን ጠርቶ፡ የዓለም ካርታውን መልሳ÷ እንደ ነበረ አድርጋ÷እንድታጋጥም አዞአት፡-ወደ ክፍልዋ ሰደዳት።

ለጅቷ ግን ከጥቂት ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ተመልሳ እየሮጠች መጣች።ከዚያም በሚገባ የተጋጠመውን የዓለም ካርታ ለአባቷ አቀበለችው።

እርሱም ትንሽ ልጅ ሆና እያለች ቁርጥራጩን የዓለም ካርታ እንዲህ በቶሎ÷በማጋጠሟ እጅግ ተገረመና፡- ማሚትዬ÷እንዲህ በቶሎ የፈጸምሽው እንዴት ነው? ሲል ጠየቃት።

እርስዋም "ቀላል ነው"በማለት መልስዋን ቀጠለችና፡- "አላየኸውም እንጂ ከዓለሙ ካርታ በስተ ጀርባ የየሱስ ሥዕል አለበት።ስለዚህ ኢየሱስን ቦታውን ሳስይዘው፡- ዓለም አውቃ ቦታዋን ይዛ ቁጭ አለች።" ስትል መለሰችለት።ዕውነትም ኢየሱስ የጌትነት ቦታውን ሲይዝ÷ ሁሉም ነገር አውቆ ቦታውን ይይዛል። አንተስ? ኢየሱስ በሕይወትህ የጌትነቱን ቦታ ይዞአል?

# ደኅንነትና ምስክርነት

ኢየሱስ ወደ ጀልባው በመግባት ላይ ሳለ አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው 'እባክህ ልከተልህ' ብሎ ለመነው፡፡ ኢየሱስ ግን አልፈቀደለትም፤ነገር ግን "ወደ ቤትህ ሂድና ጌታ ምን ያክል ታላቅ ነገር እንደ አደረገልህና እንዴትስ እንደማረህ ለቤተ ሰብህ አውራላቸው" አለው፡፡ ሰውየውም ኢየሱስ ያደረገለትን ነገር "አሥር ከተሞች" በሚባል አገር ማውራት ጀመረ፤የሰሙትም ሁሉ ይደነቁ ነበረ፡፡ (የማርቆስ ወንጌል 5÷18–20 አዲሱ ትርጉም)

ጌታ ኢሱስ አንድን ሰው ነፃ ሲያወጣው በግልጽ ይታወቃል፡፡ ሰው ከኃጢአት ሆነ ከአጋንንት ነፃ ሲወጣ በፍጹም መደበቅ አይቻልም፡፡ ከዚህ በላይ ታሪኩን ያነበብነው የጌራስኖን ሐገር ሰው፡– ከብዛታቸው የተነሣ ሌጊዎን (ሠራዊት) ከተባሉት የአጋንንት መንጋ ነፃ ሲወጣ፥ በከተማውም ሆነ በከባቢው በሚኖሩት ሁሉ ዘንድ ፈጥኖ ተሰማ፡፡ብዙ ሰዎችም የሰሙትን ለማረጋገጥ ወደ ሥፍራው እንደ ሄዱ ከመጽሐፍ እናነባለን፡፡

ዛሬም እግዚአብሔር ሰውን ከእስራት ሲፈታ እንዲሁ ይሆናል፡፡ ወዳጅና ዘመዶች ወዲያው ያውቃሉ፡፡ የመሸታ ጓደኞች ወዲያው ያውቃሉ፡፡ የሥራ ጓደኞች ወዲያው ያውቃሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም እንዲሁ ሲመላለስ የነበር ሰው መፈታትን ሲያገኝ፡– ክርስቲያኖቹ ወዲያው ልዩነት ያያሉ፡፡ ጎረቤቶችም ብዙ ሳይቆይ ይረዳሉ፡፡

እግዚአብሔር አድኖህ ከሆነ፥ለመመስከር አትፈር! እግዚአብሔር ስላደረገልህ ነገር ደስ ብሎህ ለሌሎች መናገርህ ምስክርነትህ ነውና፡፡ እግዚአብሔር ከአንተ የሚጠብቀው ደኅንነትህን ብቻ አይደለም፡፡ ቢሆንማ ኖሮ፡–ንስሐ ገብተህ ከዳንህ በኋላ ወዲያው ከዚህ ዓለም በወሰደህ ነበረ፡፡ ነገር ግን ከዳንህ በኋላ ምስክሩ እንድትሆንለት ይፈልጋል፡፡የምመሰክረው የትነው ትል ይሆናል፡፡ እዚሁ ባለህበት ቦታ ነው፡፡ አብረውህ በቤትህና በጐረቤትህ እንዲሁም በመሥሪያ ቤትህ ወይም በትምሕርት ቤትህ ላሉት ነው፡፡

ከአጋንንት ነፃ የወጣው ሰው ከየሱስ ለመለየት አልፈለገም፡፡ስለዚህ በጀልባው ተሳፍሮ አብሮት ለመሄድ ለመነ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን አልፈቀደለትም፡፡ ለምን? በትውልድ ሐገሩ፥<u>በሚያውቃቸው ሰዎች ፊት ምስክር እንዲሆንለት ስለ ፈለገ ነው</u> የዚህ ሰው አገልግሎት በአጋንንት በሚሰቃይበት በመቃብር ቦታ አይደለም፡፡ በሲቃይ በሚራወጥበት በተራራውም ላይ አይደለም፡፡ነገር ግን በአጋንንት ከመያዙ በፊት በኖረበት በከተማው ነበረ፡፡

ጌታን ከተቀበልን በኋላ ከማያምኑት ተነጥለን ወይም ተመሳስለን፡– ዕምነታችንን ደብቀን እንድንኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ የሰፈነበት የመነቃቃት ስብሰባ ላይ ስንካፈል፥ ቶሎ ባያበቃና እዚያው ብንቆይ የሚያሰኝበት ጊዜ አለ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ከክፉ መናፍስት እስራት የፈታው ሰው ሁኔታ እንደዚሁ ነው፡፡ የየሱስ መገኘት ማለት መፈታትና ደኅንነት ማለት ስለ ሆነለት ነው፡፡

ጌታ እግዚአብሔር በየጊዜው ብዙ ቅብዓትና መንፈሳዊ በረከት ወደ አለበት ወደ መገኘቱ ከፍታ ያወጣናል፡፡ ከዚያም ልክ ጌታ ኢየሱስ ከአጋንንት ለነፃው ሰው እንዳለው፡– "ወደ ቤትህ ሂድ" ይለናል ፡፡

እግዚአብሔር በየት ቦታ ምስክሩ እንድትሆንለት እንደሚፈልግህ በጸሎት ጠይቀው፡፡ ነገር ግን እዚያው ባለህበት ቦታ ለቤተሰብህ፥ለጐረቤትህ፥በመሥሪያ ቤትህ መስክርልኝ እንደሚልህ አልጠራጠርም፡፡

# መንግሥተ ሰማይ

ሰው መንግሥተ ሰማይ መግባቱን፡– በሕይወት እያለ፡ ማወቅ ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ምን ይላል? ለመሆኑ እንዲህ ያለ ነገር በቀደመው የግዕዝ መጽሐፍ ተጠቅሶአል? እስቲ እንመልከት፡–

ወዛቲ፡ይእቲ፡ስምዑ፡ለእግዚአብሔር፡አንተ፡ወሀበነ፡ሕይወተ፡ዘለዓለም፡ወዛቲ፡ይእቲ፡ሕይወት፡አንተ፡በወልዱ፡፡ዘሀለወ፡ምስሌሁ፡ወልድ፡ቦቱ፡ሕይወት፡ወዘሰ፡ኢሀሎ፡ምስለ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡አልቦቱ፡ሕይወት፡፡ወዘንተ፡ጸሐፍኩ፡ለክሙ፤ከመ፡ታእምሩ፡ከመ፡ብክሙ፤ሕይወት፡ዘለዓለም፡እለ፡ተአምኑ፡በስሙ፡ለወልደ እግዚአብሔር፡፡ *(፩ዮሐንስ ም ፭ ፲፩–፲፫)*

*(ግዕዝ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ማሳተሚያ 1975 ዓ/ም ሐዲስ ኪዳን እትም)*

*"እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው ፡፡ <u>ልጁ ያለው ሕይወት አለው፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡ያዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ፡</u>* በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ፡፡" (1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5÷11–13)

*ከዚህ ከመጨረሻው ዐረፍተ ነገር የምንረዳው <u>በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ</u> ማወቅ ትችላላችሁ የሚል መልእክት ነው፡፡ የግዕዙን መጽሐፍ የጠቀስሁበት ምክንያት አንዳንድ ጊዜ የዳግማዊ ልደት ጉዳይ በዘመኑ ክርስቲያኖች የተጀመረ "ዘመን አመጣሽ" አነጋገር መስሎ ሲወሰድ ስለሚታይና በዚህ የሚጠቀም ሰው ሊኖር እንደሚችል በማሰብ ነው፡፡*

*ሌላም ብዙዎች የሚሰናከሉበት "ዘመናዊ" መሰል ነገር ብንጨምር መልካም ነው፡፡ እርሱም <u>ጌታን መቀበል</u> የተባለው ነው፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ከግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ከቁጥር 11 እና 12 እንደሚከተለው እንመልከት፡–*

*"ውስተ፡ዚአሁ፡መጽአ፡ወእሊአሁሰ፡ <u>ኢተወክፍዎ</u> ፡፡ ወለእለሰ፡<u>ተወክፍዎ</u>፡ወሀቦሙ፡ ሥልጣነ፡ውሉደ፡እግዚአብሔር፥ ይኩኑ፡ለእለ፡አምኑ፡በስሙ፡፡" ወንጌለ ዮሐንስ ፩÷ ፲፩ – ፲፪*

እዚህ ላይ የመጀመሪያውን ጥያቄአችንን ልመልስና፡– <u>ሰው በምድር ላይ እያለ መንግሥተ ሰማይ መግባቱን ማወቅ ይችላል</u>፡፡ ሚስጢሩም በእግዚአብሔር ማመኑ ወይም በኢየሱስ ማመኑም ብቻ አይደለም፡፡ መጽሐፍ እንደሚል አጋንንትም ያምናሉ፡፡ ይንቀጠቀጡማል፡፡ የዘላለም ሕይወት ሚስጢሩ ያለው በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቁጥር 11 እና 12 በግዕዝ በጠቀስሁት ላይ ነው፡፡ ይህንኑ በአማርኛ ስንጠቅሰው እንዲህ ይላል፡–"የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥የገዛ ወገኖቹም <u>አልተቀበሉትም</u>፡፡ <u>ለተቀበሉት</u> <u>ሁሉ</u> ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ <u>የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው</u>" ይልና "እነርሱም <u>ከእግዚአብሔር ተወለዱ</u> እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም፡፡" በማለት <u>ኢየሱስን መቀበልንና ከእግዚአብሔር መወለድን</u> በአንድነት ያቀርባል፡፡

*(እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ፣ መንግሥተ ሰማይ ወራሽ መሆኑን ያላረጋገጠ፥ ይህንን ጽሑፍ የሚያነብ ሰው ሁሉ የነፍሱን ነገር ቸላ በማለት በራሱ ላይ እንዳይፈርድ እንድትረዳ በኢየሱስ ቅዱስ ስም እለምንሃለሁ፡ አሜን፡፡)*

*እንግዲህ ወራሽ ለመሆን፥የልጅነትን ሥልጣን መቀበል ወይም ልጅ ሆኖ መወለድ ሕጋዊ ግዴታ ነው፡፡"ለተቀበሉት ሁሉ… የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው…"፡፡ ስለሚል ሰጦታውን የሚያምን "ያምናል"፡፡ ያመነና <u>የተቀበለ</u> ግን ስለ ተቀበለ ለራሱ ሥልጣን አለው፡፡ ሥልጣኑም የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ነው፡፡ ልጅ ከሆንህ መውረስ የሚከለክልህ የለም፡፡*

## *መንግሥተ ሰማይ መግባቴን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ አለብኝ ?*

**በመጀመሪያ**፡– እግዚአብሔር እንደሚወድህ ዕመን፡– "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ <u>ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና</u>፡፡" (የዮሐንስ ወንጌል 3÷16)

**ቀጥሎም** ኃጢአተኛ መሆንህን እመን፡– "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ (ወደ ሮሜ ሰዎች 3÷23)

**ከዚያም**፡– ስለ ኃጢአትህ ዋጋ ሞት የተገባህ መሆኑን የተጻፈውን እወቅ፡– "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና…" (ወደ ሮሜ ሰዎች 6 ÷ 23)

**የኃጢአትህን ዕዳ** ኢየሱስ በመስቀል ሞቱ እንደ ፈጸመልህ እወቅ፡– "ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና፡፡" (ወደ ሮሜ ሰዎች 5÷6)

**ቀጥሎም**፡–

መጽሐፍ እንደሚል እግዚአብሔር ወልድ የሆነው ኢየሱስ ያደረገልህን መስዋዕትነት በእምነት መቀበል አለብህ፡፡ <u>"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም</u> ፡፡" (የዮሐንስ ወንጌል 3÷36)

**በመጨረሻም**፡– በዕውነት ከተቀበልህና ካመንክበት መስክርለት!! "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር፡ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ <u>ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና</u>፡ <u>በአፉም መስክሮ ይድናልና</u> ፡፡" (ወደ ሮሜ ሰዎች 10 ÷ 9 እና 10)

## የንስሐ ፀሎት፡–

**ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአቴ እንደ ሞተ፡ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው አምናለሁ፡፡ መድሃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ÷ የግሌ <u>ጌታና አዳኝ</u> አድርጌ እቀበላለሁ፡፡ አንተም እንደ ተስፋ ቃልህ፥በተባረከው መንግሥትህ ተቀበለኝ፡፡ አሜን ፡፡**

(ይህንን ፀሎት ለመጀመሪያ ጊዜ ከፀለያችሁ ፡ ወይም ኢየሱስን ስለ መቀበል ጥያቄ ቢኖራችሁ ከሚከተሉት አድራሻዎች ባመቻችሁ ጻፉልን፡፡)


hello@ethiogodslove.org (e-mail)

God's Love
P.O.Box 6734
L.S. MO 64064 (USA)

የዌብ ገጻችንን ለመጎብኘት
www.ethioGodslove.org


ኢየሱስ ጌታ ነው፡፡ ጌታ ይባርክህ፡፡